በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 203206

ህዳር 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡-አቶ ወንድወሰን ፍልፍል -- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ወይንሸት ወ/ገብርኤል- አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መሃል ያለውን የአፈፃፀም ክርክር አስመልክቶ የሰጠው ትዕዛዝ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤት መፅናቱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይኸው ስሕተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ሲሆን አመልካች በስር ፍርድ ቤት የፍርድ ባለዕዳ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ነበሩ፡፡

በግራ ቀኙ መሃል ባለው የሰሌዳ ቁጥር 2-38101 አአ መኪናን አስመልክቶ አመልካች ህዳር 09 ቀን 2013 ዓም በተፃፈ አቤቱታ አከራካሪው መኪና አቶ ደጀኔ ዘውዴ ለተባሉ አድራሻቸው ግንደበረት ከተማ ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 238 ነዋሪ ለሆኑት የተሸጠ መሆኑን ገልፀው የፌደራል ፖሊስ በዚህ አድራሻ ፈልጎ እንዲያመጣ እንዲታዘዝላቸው የጠየቁ ሲሆን ይህንን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ በሰጠው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ትዕዛዝም አመልካች መግለፅ ያለባቸው አሁን መኪናው ያለበትን መሆኑን፤መኪናው ስለመሸጡ ፍርድ ቤቱ በዋናው ውሳኔ ላይም ያልገለፀ መሆኑን፤መኪናው ተንቀሳቃሽ ከመሆኑ አንፃር አመልካች መኪናው ያለበትን የመግለፅ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን መነሻ በማድረግ አመልካች መኪናውን የያዘውን ግለሰብና አሁን ያለበትን ለፌደራል ፖሊስ እንዲያሳዩና ፌደራል ፖሊስም ተሸከርካሪውን በተገኘበት በመያዝ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም መኪናውን ከ7 አመት ከ1 ወር በፊት በ06/05/2006 ዓም በተፈረመ ውል ለአቶ ደጀኔ ዘውዴ ጫላ በሽያጭ አስተላልፌ አስረክቤ እያለ ፤ውሳኔው ሲሰጥም መኪናው በእኔ እጅ ባልነበረበት ፤ገዢው መኪናውን ገዝተው ከተረከቡ በኋላ የት እንደወሰዱት የማውቀው ነገር በሌለበት ፤መኪናውን ማቅረብና ውሳኔውን መፈፀም አለብህ በማለት የተሰጠው ትዕዛዝ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.392(1) እና (2) እንዲሁም በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 69471 እና 29344 የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ የሚፃረር በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች መኪናውን የሸጡ መሆኑንና የሸጡለትንም ግለሰብ አድራሻ ለፍርድ ቤቱ አስረድተው በፖሊስ እንዲቀርብለት እየጠየቁ አመልካች መኪናውን ካለበት እንዲያቀርቡ የታዘዘበትን አግባብ ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስም የፍቺ ክርክሩን በያዘው ፍርድ ቤት መኪናው እንዳይሸጥ ታግዶ ስለነበረ በዚህ ምክንያትም ስም ለማዛወር ስለማይችሉ ሆን ብለው ቀኑን ወደ ኋላ በማድረግ በጋብቻ ውስጥ እንደተሸጠ በማድረግ ያቀረቡት እንጂ መኪናው ጋብቻ ውስጥ እያለን ያልተሸጠ በመሆኑ፤የመኪናው መሸጥ በዋናው ክርክር ጊዜ ያልተነሳ በመሆኑ አሁን እንደ አዲስ ሊነሳ ስለማይችል፤መኪናው የተሸጠ ከሆነ የጋራ ሀብት ተብሎ ሲወሰን በይግባኝ ያላሻረው ስለሆነ ፤መኪና ተሸጠ የሚባለውም ስመሀብቱ ሲዘዋወር በመሆኑና የመኪናው ስም ያልተዛወረ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፡ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ፍርዱን የሚያስፈፅመው ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈፀም ተስማሚ ነው ብሎ የሚገምተውን ትዕዛዝ የመስጠት ስልጣን ያለው መሆኑን የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.392(1) ያመለክታል፡፡አከራካሪው መኪና መሸጡን ጠቅሰው የገዢውን አድራሻ ጭምር በማመልከት መኪናው በፖሊስ ተፈልጎ እንዲቀርብ ህዳር 09 ቀን 2013 ዓም በተፃፈ አቤቱታ ያመለከቱት አመልካች መሆናቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡አመልካች በዚህ አግባብ አፈፃፀሙ በአከራካሪው መኪና ላይ እንዲቀጥል ካመለከቱ በኋላ መኪናው ያለበትን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አሁናዊ አድራሻ ለፖሊስ እንዲያሳዩ በችሎቱ ሲታዘዙ አመልካች ሀሳባቸውን በመቀየር በመኪናው ላይ ፍርዱ ሊፈፀም አይችልም በማለት የተከራከሩበትን በቂና አሳማኝ ምክንያት በክርክራቸው ላይ አላመለከቱም፡፡

በገዛሁት መኪና ላይ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም በማለት የመከራከሩ ድርሻ መኪናውን በእርግጥም ገዝተው መብታቸውን አረጋግጠው ከሆነ የገገርው ድርሻ ሆኖ እያለ አመልካች መኪናውን ገዝተዋል የሚሏቸውን ሰው አላግባብ በመወከል መኪናው ላይ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የለም በማለት ህዳ 09 ቀን 2013 ዓም ካቀረቡት አቤቱታ በተቃራኒ መከራከራቸው አሳማኝ ሆኖ ስላላገኘነው በዚህ አግባብም በአከራካሪው መኪና ላይ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች መኪናው የሚገኝበትን አሁናዊ አድራሻ ለፖሊስ እንዲያመለክቱ ማዘዙና ይህ ትዕዛዝ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መፅናቱ የሚነቀፍ ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ.86371 በቀን 08/03/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው የአፈጻፀም ትዕዛዝና ይህንን ትዕዛዝ በማፅናት የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.257832 ጥር 20 ቀን 2013 ዓም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

**<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>**

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም